# የ ህዝብ ቆጠራ ማጭበርበርን መለየት

## የፖስታ መልእክት

የ ህዝብ ቆጠራ ቢሮ የፖለቲካ ፓርቲን በመወከል የእርስዎን የማህበራዊ ደህንነት ቁጥር፣ ገንዘብ ወይም ምንም ነገር አይጠይቅም።

የ 2020 ህዝብ ቆጠራ፣ የአሜሪካ ማህበረሰብ ዳሰሳ እና ሌሎች የ ህዝብ ቆጠራ ቢሮ ዳሰሳዎች መመለሻ አድራሻቸው ጄፈርሰንቪል፣ ኢንዲያና ነው።

ህጋዊ የሚመስል ሰነድ ከፖስታ ከተቀበሉ ነገር ግን ከላይ ያሉትን የሚጠይቅ ከሆነና አጠራጣሪ መመለሻ አድራሻ ካለው ይጣሉት!

## በአካል ወይም በስልክ

የ ህዝብ ቆጠራ ቢሮ ሰራተኞች የሚከተሉትን በፍጹም አያደርጉም፡

- ቤትዎ ውስጥ ለመግባት አይጠይቁም፤
- የባንክዎን ወይም የክሬዲት ካርድዎ ሙሉ ቁጥር አይጠይቁም፤
- የእናትዎን አባት ስም አይጠይቁም፤ ወይም
- የማይተባበሩ ከሆነ እንደሚታሰሩ አያስፈራሩም።

የ ህዝብ ቆጠራ ቢሮ ሰራተኛ ነኝ የሚል ሰው ካለ እና መረጃዎን የሚጠይቅ ከሆነ፣ መታወቂያቸውን ለማየት ጠይቁ። ፎቶ ግራፋቸውን፣ ስማቸውን፣ የኮሜርስ ዲፓርትመንት አርማ ምልክት እና አገልግሎት ማብቂያ ቀን ሊኖረው ያስፈልጋል።

መረጃቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ስልኩን ይዝጉትወይም በሩን ይዝጉት!

## ኦንላይን

ህጋዊ የ ህዝብ ቆጠራ ቢሮ ኢሜይሎች እና ሊንኮች ሁልጊዜ “census.gov” ዶሜይን ያላቸው ሲሆን በሚስጥር የተያዙ ናቸው። የ ህዝብ ቆጠራ ቢሮ እርስዎን በኢሜይል ለማግኘት በፍጹም አይሞክርም።

ከ ህዝብ ቆጠራ ቢሮ ነው የሚል ኢሜይል ከደረሰዎት እና ኢሜይል አድራሻው መጨረሻ “.com” ከሆነ እና አጠራጣሪ ሊንኮች ካሉት፣መልስ አይመልሱ ወይም ምንም ሊንኮች አይክፈቱ! ያጥፉት ወይም ወደሚከተለው አድራሻ ይላኩት ois.fraud.reporting@census.gov

ሁልጊዜ በማሰሻው መስኮት ላይ “https://” ወይም የቁልፍ ምልክት ይመልከቱ።

https://census.gov

## ለማረጋገጥ እርዳታ ይፈልጋሉ?

ለማረጋገጥ የሎስ አንጀለስን የአካባቢ ቆጠራ ቢሮ በ 1-800-922-3530 ያግኙ፡
(1) ደዋይ/በበርዎ ላይ ያለው ሰው የ ህዝብ ቆጠራ ቢሮ ሰራተኛ ነው፤ ወይም
(2) መልስ ከመመለስዎ በፊት የዳሰሳ ኢሜይል ሊንክ ወይም ደብዳቤ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ።


የዋሺንግተን ግዛት ዋና አቃቢ ህግ ቢሮ
የሸማች ጥበቃ ክፍል
www.atg.wa.gov/consumer-issues

AM Amharic

ATTORNEY GENERAL OF WASHINGTON

ጥያቄ ወይም ጥርጣሬ አለዎት?
**በ 1-800-551-4636 ይደውሉልን**